ጎሕ ቤቶች ባንክ
GOH BETOCH BANK

የጎሕ ቤቶች ባንክ አክሲዮን ማኅበር
የባለአክሲዮኖች 1ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ
ቃለ-ጉባዔ

Federal Documents Authentication & Registration Agency Addis Ababa (Branch Tweleve Office)

ሕዳር 28 ቀን 2014 ዓ.ም.
አዲስ አበባ

ጎሕ ቤቶች ባንክ
GOH BETOCH BANK

ሕዳር 28 ቀን 2014 ዓ.ም.

የጎሕ ቤቶች ባንክ አክሲዮን ማኅበር

የባለአክሲዮኖች 1ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ

ቃለ-ጉባዔ ቁጥር 1

1. **ጠቅላላ ጉባዔው የተደረገበት ቦታ፣ ቀንና ሰዓት**

   1.1. **ቦታ፡-** በኢንተር ሌግዠሪ (በቀድሞ ኢንተርኮንቲኔንታል አዲስ) ሆቴል የመሰብሰቢያ አዳራሽ፤

   1.2. **ቀን፡-** ሕዳር 28 ቀን 2014 ዓ.ም.

   1.3. **ሰዓት፡-** ከጠዋቱ 2፡00 እስከ 5፡30

2. **የጉባዔው ጥሪ አደራረግ፣**

ይህ የባለአክሲዮኖች 1ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ የተጠራው በአዲሱ ንግድ ሕግ አዋጅ ቁጥር 1243/2013 አንቀፅ 367 እና 370 መሠረት ከጉባዔው ዕለት 24 ቀናት አስቀድሞ ማክሰኞ ጥቅምት 30 ቀን 2014 ዓ.ም. ታትሞ በወጣው አዲስ ዘመን ጋዜጣ እና በተለያዩ ቀናት በፋና ኤፍ ኤም 98.1፣ አሃዱ ኤፍ ኤም 94.3 እና ሸገር ኤፍ ኤም 102.1 ሬዲዮ ጣቢያዎች በተላለፉ የሬዲዮ ማስታወቂያዎች ነው፡፡

3. **ድምፅ ቆጣሪዎች፣ በጉባዔው የተገኙ/ያልተገኙ የባንኩ ዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት እና ታዛቢዎች**

3.1. የጉባኤዉ ድምፅ ቆጣሪዎች

ጉባዔው ሥራውን ከመጀመሩ በፊት በአዲሱ የንግድ ህግ አንቀጽ 379 መሰረት የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ የሆኑት አቶ ጌታሁን ናና የጉባዔው ሰብሳቢ ሆነው ከተሰየሙ በኋላ በንግድ ሕግ አንቀጽ 380 መሠረት በጉባዔው ላይ ከተገኙት የባንኩ ከፍተኛ ባለአክሲዮኖች መካከል ድምፅ ቆጣሪ የሚሆኑ ባለአክሲዮኖችን በስምምነት እንዲመርጡ ጠየቁ፡፡ በጉባዔው ከፍተኛ ባለአክሲዮን የሆኑ እያንዳንዳቸው እኩል ብር 50 ሺህ አክሲዮኖች የያዙ ስድስት የማህበሩ አባላት ተገኝተዋል። እነዚህ ከፍተኛ ባለአክሲዮኖች በስምምነት ከመካከላቸዉ አቶ አድማሱ ጠና (ተወካይ አቶ ጌቱ ድንቁ) እና ወይ. ያስሚን ፈይሰል ድምፅ ቆጣሪ እንዲሆኑ መረጡ። በተጨማሪም በንግድ ህግ አንቀጽ 340 መሰረት የማህበሩ ፀሐፊ የሆኑት ወይዘሮ መስከረም መለሰ በንግድ ህግ አንቀጽ 341 (5) መሰረት የጉባዔውን ቃል-ጉባዔ እንዲይዙ ተመደቡ።

3.2. በጉባዔው ላይ የተገኙ ዳይሬክተሮች፣

መስከረም 28 ቀን 2013 ዓ.ም በተደረገው የፈራሚዎች ጉባኤ በዳይሬክተሮች ቦርድ አባልነት ተመርጠዉ ባንኩን እያገለገሉ ያሉና በዛሬዉ ዕለት በጠቅላላዉ ጉባኤ ላይ የተገኙት የሚከተሉት ናቸዉ፡፡

በጉባኤዉ ላይ የተገኙ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ዝርዝር

ተ/ቁ	ስም	ኃላፊነት	በተወካይ ከሆነ የተወካይ ዳይሬክተር ስም
1	አቶ ጌታሁን ናና ጀንበር	ሰብሳቢ	
2	አቶ ገ/የሱስ ኢጋታ ሲማ	ም/ሰብሳቢ	
3	ዶ/ር ኢ/ር ውብሸት ዠቅአለ መንገሻ	አባል	
4	ወ/ሮ ፋሲካ ከበደ ተመስለዉ	አባል	
5	አቶ ከፈኒ ጉርሙ ገመዳ	አባል	
6	ወ/ሮ ፅዮን አድማሱ በየነ	አባል	

7	ኢትዮ ላይፍና ጄኔራል ኢንሹራንስ አ.ማ. ተወካይ አቶ ሺመልስ ገ/ጊዮርጊስ ሰብስቤ	አባል	
8	አቶ በላቸዉ ሁሪሳ ዳዲ	አባል	
9	ሬድዋ ሞተርስ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ተወካይ አቶ ታደሰ አድማሱ ጠና	አባል	

3.4. በጉባዔው ላይ የተገኙ ታዛቢዎች

የሚከተሉት ሰዎች እንደመጡበት ተቋም ሥልጣንና ተግባር ተቋማቸዉን በመወከል በታዛቢነት በጉባኤዉ ላይ ተገኝተዋል፡፡

ተ/ቁ	ስም	የወከሉት ተቋም
1	አቶ ተመስገን መንዛ	የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ
2	አቶ አብርሃም ብርሃኑ	የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ
3	አቶ ኦንኬ ጮሎፎ	የፌደራል የሠነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ኤጀንሲ

4. ምልዓተ ጉባዔ

የጉባኤዉ ሰብሳቢ በንግድ ሕጉ አንቀፅ 374 እና 402 መሠረት የዕለቱ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ለማካሄድ የሚያስችል ድምፅ መገኘቱን እንዲያረጋግጡ ድምፅ ቆጣሪዎችን የጠየቁ ሲሆን ድምፅ ቆጣሪዎችም አስፈላጊዉን የቆጠራ ሂደት በመከተልና በማጣራት የሚከተለዉን ሪፖርት ለጉባኤዉ አቅርበዋል፡፡

4.1. ጠቅላላ የማኅበሩ ባለአክሲዮኖች ብዛት፡ 6,657

4.2. ጠቅላላ የማኅበሩ የተፈረመ አክሲዮን ብዛትና ጠቅላላ ዋጋቸዉ፡- ቁጥራቸዉ 1,056,210 የሆኑ በድምሩ ብር 1,056,210,000.00 ዋጋ ያላቸዉ አክሲዮኖች፤

4.3. በዕለቱ በስብሰባው የተገኙ አባላትና የያዙት አክሲዮን ብዛት፡- 389,808 (36.91 በመቶ) አክሲዮኖችን የያዙ ቁጥራቸዉ 121 የሆኑ ባለአክሲዮኖች[1]፤

4.4. በዕለቱ በስብሰባው ያልተገኙ አባላትና የያዙት ብዛት፡- 666,402 (63.09 በመቶ) አክሲዮኖችን የያዙ ቁጥራቸዉ 6,536 የሆኑ ባለአክሲዮኖች፤

4.5. ለጉባዔው አስፈላጊ የሆነ የአክሲዮን ብዛትና መቶኛ፡ 352,070 አክሲዮኖች (33.33333%)

በዚሁ መሠረት በንግድ ሕግ አንቀጽ 402(4) መሠረት ከማኅበሩ ባለአክሲዮኖች 389,808 አክሲዮኖችን (36.91%) የሚወክሉ አባላት የተገኙ ስለሆነ በጉባዔው አጀንዳ ላይ ተወያይተው ውሣኔ የማሳለፍ ሥልጣን ያላቸው መሆኑ ተረጋግጦ ጉባዔው ስብሰባውን ጀምሯል፡፡

5. የጉባዔው አጀንዳዎች

5.1. ድምፅ ቆጣሪዎችን መሰየም፣

5.2. የጉባኤዉ ምልዐተ ጉባኤ መሟላቱን ማረጋገጥ፣

5.3. የጉባኤዉን አጀንዳ ማፅደቅ፣

5.4. የማህበሩን የተፈረመ ዋና ገንዘብ አከፋፈል ጊዜና ሁኔታ በተመለከተ ተወያይቶ መወሰን፣

---

[1] ጉባዔዉ ከተጀመረ በኋላ ሌሎች ባለአክሲዮኖች ለመሳተፍ የመጡ ሲሆን በጉባኤዉ ላይ የተሳተፉ ጠቅላላ ባለአክሲዮኖች ብዛት 143 ደርሷል፤ ያላቸዉ ጠቅላላ የአክሲዮን ቁጥርም 419,358 (39.7%) ሆኗል፡፡

5.5. የማህበሩን ዋና ገንዘብ ማሳደግና ዋና ገንዘቡ የሚያድግበት ሁኔታ መወሰን፣

5.6. የማህበሩን የመተዳደሪያ ደንብ እና የመመሥረቻ ፅሑፍ ማሻሻል፣እና

5.7. የጉባኤዉን ቃለ ጉባኤ ማፅደቅ፤

ናቸዉ፡፡

6. የጉባዔው ውይይት አጭር ቃልና ውሣኔ፣

ከላይ በአጀንዳ ቁጥር 5.1 እና 5.2 የተመለከቱት ጉዳዮች በተራ ቁጥር 4 ሥር በመጠናቀቃቸው ጉባኤው ወደ ቀሪዎቹ አጀንዳዎች አመራ።

6.1 የጉባኤዉን አጀንዳ ማፅደቅ

የጉባኤው ሰብሳቢ ከላይ ከቁጥር 5.4 እስከ 5.7 የተመለከቱትን አጀንዳዎች ለጉባዔው በንባብ ከአሰሙ በኋላ ጉባዔው ተቀብሎ እንዲያፀድቅ ጠየቁ። ጉባዔውም አጀንዳዎቹን ተቀብሎ በሙሉ ድምጽ አፀደቀ።

6.2. የማህበሩን የተፈረመ ዋና ገንዘብ አከፋፈል ጊዜና ሁኔታ በተመለከተ ተወያይቶ መወሰን፣

የባንኩን የተፈረመ ዋና ገንዘብ የመክፈያ ጊዜ ማሳጠር እና ካፒታል ማሳደግ አስፈላጊ የሆነበትን ምክንያት በማስመልከት የጉባዔው ሰብሳቢ መግለጫ ሰጥተዋል፡፡ በመግለጫቸውም:-

ሀ. በአሁኑ ጊዜ ያለዉ የባንኩ የተፈረመ ዋና ገንዘብ/ካፒታል ብር 1,056,210,000 ነው። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ባወጣዉና ከሚያዝያ 04 ቀን 2013 ዓ.ም. ጀምሮ ተፈጻሚ በሆነዉ መመሪያ ቁጥር SBB/78/2021 መሠረት የባንኮች ዝቅተኛ የተከፈለ ዋና ገንዘብ (ካፒታል) መጠን ብር 5 ቢሊዮን መሆን አለበት፡፡ ይህን አስገዳጅ ዝቅተኛ የተከፈለ ዋና ገንዘብ መጠን፤

- ነባር ባንኮች በ5 ዓመት ውስጥ፤
- እንደእኛ በወቅቱ በመመስረት ሒደት ላይ የነበሩ ባንኮች ደግሞ የባንክ ሥራ ከጀመሩበት ቀን ጀምሮ በ7 ዓመት ውስጥ፤

ማሟላት አለባቸው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ባንኮች በተሰጠዉ ጊዜ ውስጥ ዝቅተኛዉን የዋና ገንዘብ መጠን የሚያሟሉበትን ሁኔታ በተመለከተ የድርጊት መርሐግብር (action plan) አዘጋጅተዉ ለብሔራዊ ባንክ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

ስለሆነም ጎሕ ቤቶች ባንክ በህግ የተቀመጠውን ዝቅተኛ የካፒታል መጠን ብር 5 ቢሊዮን ለማሟላት እስከ ጥቅምት 2021 ዓ.ም. ድረስ ቢያንስ ብር 3.95 ቢሊዮን የሚያወጡ አዲስ አክሲዮኖችን መሸጥ ያለበት በመሆኑ፤

ለ. ባንኩ የሞርጌጅ ባንክ ስለሆነ አትራፊ ሆኖ ለመቀጠል ከፍተኛ ካፒታል ስለሚያስፈልገዉ፤

ሐ. ባንኩ ተከታታይ ዕድገት እና ትርፋማ ይሆን ዘንድ ከታሰበው ዕድገት ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ስጋትን ሊሸከም የሚችል ካፒታል ስለሚያስፈልገው፤

መ. ከነባር ባንኮች እና አዲስ ወደ ገበያው እየገቡ ካሉ ባንኮች ጋር ለመወዳደር የሚያስችል የካፒታል አቅም ለመገንባት እና

ሠ. ባንኩ በአለም አቀፍ ደረጃ ካሉ ኢንቨስተሮች (investors)፣ በሪል ስቴት ዘርፍ ከተሠማሩ እና ከአበዳሪ ተቋማት ጋር አብሮ ለመስራት ስለሚገባው እና አንዳንድ አካላት ደግሞ የባንኩን ደዋና ገንዘብ ጥንካሬ እንደመለኪያ ስለሚያቀርቡ ለዚህ በቂ ሆኖ ለመገኘት፤

መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡

አያይዘውም የጉባዔው ሰብሳቢ የባንኩን ካፒታል ለማሳደግ ደግሞ በቅድሚያ አሁን ቃል የተገባውና የተፈረመው ካፒታል ሙሉ በሙሉ ተከፍሎ መጠናቀቅ እንዳለበት የንግድ ህጉ ስለሚያስገድድ የባንኩ የተፈረመ ካፒታል በአጭር ጊዜ ተከፍሎ መጠናቀቅ እንዳለበት አስረድተዋል።

ከዚህም በመነሳት የባንኩ የተፈረመ ካፒታል ክፍያን በተመለከተ፡-

ሀ. ባንኩ ሲመሠረት ለሽያጭ የቀረቡ እና የተፈረሙ አክሲዮኖች ቀሪ ዋጋ የመክፈያ ጊዜ የመመስረቻ ፅሑፉ እና የመተዳደሪያ ደንቡ ላይ እንደተጠቀሰዉ ባንኩ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ በ18 ወራት ውስጥ (እስከ የካቲት 30 ቀን 2015 ዓ.ም ድረስ) መሆኑ ቀርቶ እስከ ሰኔ 23 ቀን 2014 ዓ.ም (እ.ኤ.አ. ጁን 30 ቀን 2022) ድረስ ባለአክሲዮኖች ሙሉ በሙሉ ከፍለዉ እንዲያጠናቅቁ እንዲወሰን፤

ለ. በተራ ፊደል ሀ ላይ በተጠቀሰዉ ጊዜ እና በሕግ መሠረት በሚሰጠዉ ተጨማሪ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ውስጥ ባለአክሲዮኖች የሚጠበቅባቸውን ክፍለው ካላጠናቀቁ አክሲዮኖቹ የባንኩን አክሲዮን ገዝተው ግን በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ኤጀንሲ ቀርበዉ ባለመፈረማቸው ወይም አስፈላጊ ሰነዶችን ባለማሟላታቸዉ ምክንያት ባለአክሲዮን መሆን ላልቻሉ ሰዎች እንዲሸጥላቸው ወይም ተጨማሪ ለመግዛት ለሚፈልጉ ሌሎች ባለአክሲዮኖች እንዲሸጥ፤

ሐ. ከላይ በተራ ፊደል ሀ እና ለ መሠረት ያልተላለፈ/ያልተሸጠ አክሲዮን ቢኖር ከዚህ በፊት ከባንኩ ጋር ምንም ዓይነት የአክሲዮን ግብይት ግንኙነት ላልነበራቸዉ የማህበሩ አባል መሆን ለሚፈልጉና በህግ ለተፈቀደላቸው ሰዎች እንዲሸጥ፤

ቦርዱ የውሳኔ ሃሳብ ማቅረቡን ሰብሳቢው ለጉባዔው ገልጸው መድረኩን ለውይይት ክፍት አደረጉ፡፡

ቦርዱ ባቀረበው የተፈረመ ካፒታል የክፍያ ጊዜ ማሳጠር ላይ ባለአክሲዮኖች ጥያቄና አስተያየት አቅርበዋል፡፡ ከእነዚህ ውስጥ ዋና ዋናዎቹ፡

- ባንኩ እንደዚህ አይነት ጥሪ ለባለአክሲዮኖች ሲያደርግ ሃሳቡን መርምሮ ለመወሰን ባለአክሲዮኖች በቅድሚያ መረጃ እንዲያገኙ ይበልጥ ተደራሽ የሆኑ የመገናኛ ዘዴዎችን ቢጠቀም፣
- የክፍያ ጊዜ ማጠሩ ጥሩ ሆኖ ሳለ መቼ መጠናቀቅ እንዳለበት ግን በግልፅ አለመቀመጡንና አዲስ አክሲዮን አወጣጡ እንዴት እንደሆነ የበለጠ ግልፅ ቢደረግ፣
- እስካሁን የተሰሩ ስራዎችና ከዚህ በሁዋላ ምን ለመስራት እንደታቀደ ለምን ሪፖርት እንዳልቀረበ ቢገለፅልን፣
- ከዚህ በፊት ቀርበዉ ያልፈረሙ ሰዎች አሁን አክሲዮን ቢሸጥላቸዉ ምን ያህል ይታመናሉ? ባይመጡስ እንዴት ይሆናል?
- ከአክሲዮን ሽያጩ ጋር አብሮ የተሰበሰበው የአገልግሎት ክፍያ ምን ላይ እንደዋለ ቢገለፅልን፣

የሚሉ ናቸዉ፡፡

የተፈረመ ካፒታል የክፍያ ጊዜ ማሳጠርን እና ሌሎች በተነሱ ሃሳቦች በተመለከተ ከባለአክሲዮኖች ለተሰነዘሩት አስተያየቶችና ጥያቄዎች የጉባዔው ሰብሳቢ በሰጡት መልስ፡

- ባንኩ ይበልጥ ተደራሽ የሆኑ የመገናኛ ዘዴዎችን ቢጠቀም ተብሎ ለተሰጠው አስተያየት ባንኩ ጥሪውን ያደረገው ሕጉ በሚያዘው መሰረት እንደሆነና አስተያየቱን/ማሳሳቢያዉን ግን እንደተቀበሉትና ለወደፊት ጥሪ በተለያዩ ተጨማሪ መንገዶች እንደሚደረግ፣
- የመክፈያ ጊዜውና የአክሲዮን አሻሻጡ ሂደት በውሳኔ ሃሳቡ ላይ በግለፅ እንደተቀመጠ፣
- ሪፖርትን በተመለከተ አስቸኳይ ስብሰባ ላይ ህጉ ሪፖርት ማቅረብ እንደማያዝና በዚህም ምክንያት ሪፖርት እንዳልቀረበ፣
- ከዚህ በፊት ቀርበዉ ያልፈረሙ ሰዎች አሁን አክሲዮን ቢሸጥላቸዉ ምን ያህል ይታመናሉ? ለተባለዉ ከዚህ በፊት አብዛኞቹ ያልፈረሙት በተለያዩ አሳማኝ በሆነ ምክንያት እንደሆነ መረዳት ስለተቻለ፡፡ ለምሳሌ በጦር ግንባር ላይ

በመሆን፣ በወሊድ ምክንያት እና በሌሎች ምክንያቶች ያልተፈረሙ ስላሉ ዕድሉ ቢሰጣቸዉ የተሻለ እንደሆነ፤ ባይመጡ ግን ጉዳዩ በሕግ አግባብ የሚታይ እንደሆነ፡፡

- ከአክሲዮን ሽያጩ ጋር አብሮ ስለተሰበሰበው የአገልግሎት ክፍያ በተመለከተም ገንዘቡ የዋለው በምስረታው ሂደት ላይ ለነበሩ የተለያዩ ወጪዎች ለምሳሌ ለቢሮ ኪራይ፣ ለቢሮ እቃች ግዢ፣ ባንኩ ለዋና መስሪያ ቤት ለተከራየው ሕንጻ ማስተካከያ፣ ለቴክኖሎጂ ግዢና ለመሳሰሉት ወጪዎች ሙሉ በሙሉ መዋሉንና ከዚህ በተጨማሪ አንዳንድ ባለአክሲዮኖች ባንኩን ለመደገፍና ለማስተዋወቅ ከግላቸው የተለያዩ ወጪዎች እንዳወጡና በባንኩ ስም እርዳታም (Donation) እንደሰጡ፤

ማብራሪያ የሰጡ ሲሆን ጉባዔው የቀረበውን የውሳኔ ሃሳብ ተቀብሎ እንዲያጸድቀው ጠይቀዋል፡፡

ጠቅላላ ጉባዔውም በቀረበው የተፈረመ ካፒታል የክፍያ ጊዜ ማሳጠር የውሳኔ ሃሳብ ላይ ውይይት ካደረገ በኋላ የሚከተለውን ውሳኔ ያለ ምንም ተቃውሞ እና ድምፀ-ታአቅቦ በሙሉ ድጋፍ/ድምጽ ተቀብሎታል፡፡

ይኸዉም:

ሀ. ባንኩ ሲመሠረት ለሽያጭ የቀረቡ እና የተፈረሙ አክሲዮኖች ቀሪ ዋጋ የመክፈያ ጊዜ የመመስረቻ ፅሑፉ እና የመተዳደሪያ ደንቡ ላይ እንደተጠቀሰዉ ባንኩ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ በ18 ወራት ውስጥ (እስከ የካቲት 30 ቀን 2015 ዓ.ም ድረስ) መሆኑ ቀርቶ እስከ ሰኔ 23 ቀን 2014 ዓ.ም (እ.ኤ.አ. ጁን 30 ቀን 2022) ድረስ ባለአክሲዮኖች ሙሉ በሙሉ ከፍለዉ እንዲያጠናቅቁ፤

ለ. በተራ ፊደል ሀ ላይ በተጠቀሰዉ ጊዜ እና በሕግ መሠረት በሚሰጠዉ ተጨማሪ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ውስጥ ባለአክሲዮኖች የሚጠበቅባቸውን ከፍለው ካላጠናቀቁ አክሲዮኖቹ የባንኩን አክሲዮን ገዝተው ግን በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ኤጀንሲ ቀርበዉ ባለመፈረማቸው ወይም አስፈላጊ ሰነዶችን ባለማሟላታቸዉ ምክንያት ባለአክሲዮን መሆን ላልቻሉ ሰዎች የመስራችነት መብታቸው ተጠብቆ እንዲሸጥላቸው ወይም ተጨማሪ ለመግዛት ለሚፈልጉ ሌሎች ባለአክሲዮኖች እንዲሸጥ፤

ሐ. ከላይ በተራ ፊደል ሀ እና ለ መሠረት ያልተላለፈ/ያልተሸጠ አክሲዮን ቢኖር ከዚህ በፊት ከባንኩ ጋር ምንም ዓይነት የአክሲዮን ግብይት ግንኙነት ላልነበራቸዉ የማህበሩ አባል መሆን ለሚፈልጉና በህግ ለተፈቀደላችው ሰዎች እንዲሸጥ ወስኗል፡፡

6.3 የማህበሩን ዋና ገንዘብ ማሳደግና ዋና ገንዘቡ የሚያድግበት ሁኔታ መወሰን፣

የጉባዔው ሰብሳቢ ከላይ በ 6.2 ሥር በተመለከቱት ምክንያቶች አሁን ያልተከፈለባቸው አክሲዮኖች ክፍያ ሙሉ በሙሉ ሲጠናቀቅ የባንኩን ካፒታል ወደ ብር 3,056,210,000.00 (ሶስት ቢሊዮን ሃምሳ ስድስት ሚሊዮን ሁለት መቶ አስር ሺህ) ለማሳደግና ይህንን ተፈፃሚ ለማድረግ ብር 2,000,000,000.00 (2 ቢሊዮን) የሚያወጡ 2 ሚሊዮን አዲስ አክሲዮኖች ለመሸጥ ቦርዱ የውሳኔ ሃሳብ ያቀረበ መሆኑን ለጉባዔው አስረዱ፡፡ በመቀጠልም ዝርዝር አፈፃፀሙ እንደሚከተለው እንዲሆን ቦርዱ ሃሳብ ማቅረቡን ገለፁ። ይኸዉም:-

ሀ. በአዲሱ የንግድ ሕግ መሠረት ባንኩ ካፒታሉን ከማሳደጉ በፊት አሁን ቃል የተገባባቸውና የተፈረሙ አክሲዮኖች ሙሉ በሙሉ እንዲከፈሉና ይህም በቦርዱ እንዲረጋገጥ፤

ለ. በተራ ፊደል ሀ የተመለከተው መሟላቱ ሲረጋገጥ ባንኩ ብር 2,000,000,000.00 (2 ቢሊዮን) ዋጋ ያላቸው 2 ሚሊዮን አዲስ አክሲዮኖች አውጥቶ ለሽያጭ እንዲያቀርብ፤

ሐ. የባንኩ ነባር ባለአክሲዮኖች ከሚወጡት አዲስ አክሲኖች ላይ ባላቸዉ ቅድሚያ የመግዛት መብት መሠረት መግዛት የሚፈልጉትን የአክሲዮን ብዛት ሽያጩ ይፋ ከሆነበት ቀን ጀምሮ በስድስት ወር ውስጥ ለባንኩ እንዲያሳዉቁና የመግዛት ፍላጎታቸዉን በሚያሳዉቁበት ጊዜ የሚገዙት የአክሲዮን ብዛት ጠቅላላ ዋጋ 25% (ሃያ አምስት በመቶ) እንዲከፍሉ፤

መ. ባለአክሲዮኖች የተመደበላቸውን አዲስ አክሲዮን ለመግዛት ሲቀርቡ ተጨማሪ አክሲዮን ለመግዛት ፈቃደኛ መሆናቸውንና የሚገዙትን ተጨማሪ አክሲዮን መጠን በሚዘጋጀው ፎርም ላይ በመሙላት እንዲያረጋግጡ፤

24/06/14

ሠ. ባለአክሲዮኖች ለመግዛት የሚፈርሙትን አክሲዮን ዋጋ እ.ኤ.አ. እስከ ጁን 30 ቀን 2025 (ሰኔ 23 ቀን 2017 ዓ.ም.) ድረስ በየዓመቱ በእኩል መጠን እየከፈሉ ሙሉ በሙሉ እንዲያጠናቅቁ፤ እና

ረ. በተጠቀሰው አኳኋን ድልድል ተደርጎ በማናቸውም ምክንያት ሳይሸጥ የቀረ እና/ወይም ተፈርሞ ሳይከፈል የቀረ አክሲዮን ቢኖር የዳይሬክተሮች ቦርድ በንግድ ሕግ 450 መሠረት እንዲሸጥ እና ከአፈፃፀሙ ጋር ውሳኔ የሚጠይቅ ማንኛውም ጉዳይ ቢኖር ሕግ በሚፈቅደው መሠረት እንዲወስንና እንዲያስፈፅም እንዲፈቀድ ጠየቁ።

በመቀጠልም መድረኩ ለውይይት ክፍት ሆኗል።

ቦርዱ ባቀረበው ካፒታል የማሳደግ የውሳኔ ሃሳብ ላይ ባለአክሲዮኖች ጥያቄና አስተያየት ያቀረቡ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ ፡-

- የተፈረመዉ ካፒታል ክፍያ በቆየ ቁጥር ባለአክሲዮኑ ክፍያዉን እንደዕዳ ስለሚቆጥረዉ ከቀረበዉ ጊዜ ቀደም ብሎ ክፍያ እንዲፈጸም ቢደረግ፣
- ሌሎች ባንኮችም አክሲዮን እየሸጡ ከመሆኑ የተነሳ የባንኩን አክሲዮን ሊገዙ የሚችሉ ሰዎች የሌሎች ባንኮችን አክሲዮን ከመግዛታቸዉ በፊት ዝቅተኛዉን የካፒታል መጠን ለማሟላት አሁኑኑ ሥራ ቢጀመር፣
- አሁን ተከፍለው ያላለቁትን አክሲዮኖች ተከፍለው እስኪያልቁ ከመጠበቅ የአዲስ አክሲዮን ሽያጭ ለምን ጎን ለጎን አይካሄድም?
- የተፈረመዉ ካፒታል አለመከፈሉ ባንኩ ሥራ እንዳይሰራ ያደርጋል ወይ?
- ባንኩ ካፒታሉን ለማሳደግ ለምን ሼር መሸጥን ብቻ መረጠ? ሌሎች አማራጮችን ለምን አላየም?

የሚሉት በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

ካፒታል ከማሳደግ የውሳኔ ሃሳብ ጋር በተያያዘ ከባለአክሲዮኖች ለተሰነዘሩት አስተያየቶችና ጥያቄዎች የጉባዔው ሰብሳቢ በሰጡት መልስ፡-

- የባንኩ ካፒታል በሶስት ምዕራፎች (phases) ከፍሎ ለማሳደግና ዝቅተኛዉን የካፒታል መጠን ለማሟላት እንደታሰበ፣ የመጀመሪያ ምዕራፍ እ.ኤ.አ. እስከጁን 30 ቀን 2022 ዓ.ም. ፣ ሁለተኛዉ ደግሞ ከጥቅምት ወር 2022 አካባቢ ጀምሮ እስከ ጁን 30 ቀን 2025 እና ሶስተኛ እስከ አክቶበር 2028 ድረስ እንዲሆን ታቅዶ ሥራ መጀመሩንና የዛሬዉ ጉባኤ ዓላማም የዚሁ ዕቅድ አካል እንደሆነ፤
- ባንኩ አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታዎችን አሟልቶ ሥራ መጀመሩን ገልጸዉ የባንኩ ባለአክሲዮኖችም በባንኩ ሊገለገሉ እንደሚችሉ፤
- የተፈረሙ አክሲዮኖች ሙሉ ለሙሉ ተከፍለው ካላለቁ ሌላ አክሲዮን መሸጥ በህግ የተከለከለ እንደሆነ፤
- ባንኩ ካፒታሉን ለማሳደግ ለምን ሼር መሸጥን ብቻ መረጠ ለተባለው አሁን አክሲዮን በመሸጥ ለመጨመር የታሰበው የካፒታል መጠን በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የተቀመጠውን አነስተኛ የካፒታል መጠን ለማሟላት እንደሆነ፤

አብራርተው፤ ጉባኤዉ የቀረበውን የውሳኔ ሃሳብ ተቀብሎ እንዲያጸድቀው ጠይቀዋል፡፡

ጠቅላላ ጉባዔውም በቀረበው ካፒታል የማሳደግ የውሳኔ ሃሳብ ላይ ተጨማሪ ውይይት ካደረገ በኋላ ቦርዱ ያቀረበውን የውሳኔ ሃሳብ ያለ ምንም ተቃውሞ እና ድምፀ-ታአቅቦ በሙሉ ድጋፍ/ድምጽ ተቀብሎታል፡፡

ይኸዉም፡-

የባንኩን ካፒታል ወደ ብር 3,056,210,000.00 (ሶስት ቢሊዮን ሃምሳ ስድስት ሚሊዮን ሁለት መቶ አስር ሺህ) ለማሳደግና ይህንን ተፈፃሚ ለማድረግ ብር 2,000,000,000.00 (ሁለት ቢሊዮን) ዋጋ ያላቸው 2 ሚሊዮን አዲስ አክሲዮኖች እንዲወጡና እንዲሸጡ ተወስኗል፡፡

በአፈጻጸም ረገድ፡-

ሀ. በአዲሱ የንግድ ሕግ መሠረት ባንኩ ካፒታሉን ለማሳደግ ለሽያጭ ከሚቀርበው አዲስ አክሲዮን በፊት ተፈርሞ ያልተከፈለው አክሲዮን ሙሉ በሙሉ በቅድሚያ መከፈሉን እንዲረጋገጥ፤

ለ. የባንኩ ነባር ባለአክሲዮኖች ከሚወጡት አዲስ አክሲኖች ላይ ባላቸዉ ቅድሚያ የመግዛት መብት መሠረት መግዛት የሚፈልጉትን የአክሲዮን ብዛት ሽያጩ ይፋ ከሆነበት ቀን ጀምሮ በስድስት ወር ውስጥ ለባንኩ እንዲያሳዉቁና የመግዛት ፍላጎታቸዉን በሚያሳዉቁበት ጊዜ የሚገዙት የአክሲዮን ብዛት ጠቅላላ ዋጋ 25% (ሃያ አምስት በመቶ) እንዲከፍሉ፤

ሐ. በመጀመሪያ ዙር ድልድል የማይሸጥ አክሲዮን ቢኖር ባንኩ በንግድ ሕግ አንቀፅ 449 መሠረት ሁለተኛ ዙር ድልድል ማድረግ እንዲችል ባለአክሲዮኖች የተመደበላቸውን አዲስ አክሲዮን ለመግዛት ሲቀርቡ ተጨማሪ አክሲዮን ለመግዛት ፈቃደኛ መሆናቸውንና የሚገዙትን አክሲዮን መጠን በሚዘጋጀው ፎርም ላይ በመሙላት እንዲያረጋግጡ፤

መ. ባለአክሲዮኖች ለመግዛት የሚፈርሙትን አክሲዮን ዋጋ እ.ኤ.አ. እስከ ጁን 30 ቀን 2025 (ሰኔ 23 ቀን 2017 ዓ.ም.) ድረስ በየዓመቱ በእኩል መጠን እየከፈሉ ሙሉ በሙሉ እንዲያጠናቅቁ፤

ሠ. በተጠቀሰው አኳኋን ድልድል ተደርጎ በማናቸውም ምክንያት ሳይሸጥ የቀረ እና/ወይም ተፈርሞ ሳይከፈል የቀረ አክሲዮን ቢኖር የዳይሬክተሮች ቦርድ በንግድ ሕግ 450 መሠረት እንዲሸጥ እና ከአፈፃፀሙ ጋር ውሳኔ የሚጠይቅ ማንኛውም ጉዳይ ቢኖር ሕግ በሚፈቅደው መሠረት እንዲወስንና እንዲያስፈፅም ጉባኤው ለቦርዱ ሙሉ ስልጣን ሰጥቶታል።

6.4. የባንኩን የመመሥረቻ ጽሑፍ እና የመተዳደሪያ ደንብ ማሻሻል፣

የጉባዔው ሰብሳቢ የካፒታል ዕድገቱን ጉባዔው መቀበሉን በመጥቀስና ከዚህ ሃሳብ አኳያ እና የባንኩን ሥራ ያበለጠ ለማቀላጠፍ ስለሚሻሻለው የመመሥረቻ ጽሑፍ እና የመተዳደሪያ ደንብ ድንጋጌዎች መግለጫ የሰጡ ሲሆን ጉባዔውም የቀረበውን የመመሥረቻ ጽሑፍ እና የመተዳደሪያ ደንብ ማሻሻያ ያለ ምንም ተቃውሞ እና ድምፀ-ታአቅቦ በሙሉ ድጋፍ/ድምጽ ተቀብሎ አፅድቋል። በዚህ ውሳኔ መሠረት የመመሥረቻ ጽሑፍ እና የመተዳደሪያ ደንብ ድንጋጌዎች እንደሚከተለዉ ተሻሽለዋል ::

ሀ. የመመስረቻ ጽሑፉ ማሻሻያ

ሀ. የመመስረቻ ፅሑፉ አንቀፅ 5(5) ድንጋጌ ተሰርዞ በሚከተለዉ ተተክቷል፡፡

5.5. "ባለአክሲዮኖች የባንኩን አክሲዮን ለመግዛት ከፈረሙት የአክሲዮን ቁጥር ጠቅላላ ዋጋ ላይ እስካሁን ያልከፈሉትን ቀሪ ገንዘብ ይህ ጉባኤ ከተካሄደበት ቀን ጀምሮ እ.ኤ.አ. እስከ ጁን 30 ቀን 2022 ድረስ ከፍለው ማጠናቀቅ አለባቸዉ፡፡ አንድ ባለአክሲዮን በዚህ በተጠቀሰዉ ጊዜ ውስጥ የፈረመዉን አክሲዮን ቀሪ ዕዳ ካልከፈለ የ15 ቀን ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፤በተሰጠዉ ተጨማሪ የማስጠንቀቂያ ጊዜም ካልከፈለ የፈረሙትን አክሲዮን ዋጋ ከፍለዉ ተጨማሪ ለመግዛት ለሚፈልጉ ሌሎች ባለአክሲዮኖች ወይም የባንኩን አክሲዮን ገዝተዉ የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ኤጀንሲ ቀርበዉ ላልፈረሙ ወይም ሌሎች አስፈላጊ ሰነዶችን ላላቀረቡ ሰዎች ይሸጣል፡፡ ይህ ሁሉ ሆኖ ያልተላለፈ/ያልተሸጠ አክሲዮን ቢኖር የማህበሩ አባል ላልሆኑ ሰዎችና በህግ ለተፈቀደላቸው ሰዎች ይሸጣል"፡፡

ለ. የመመስረቻ ፅሑፉ አንቀፅ 10 ሥር የሚከተለዉ አዲስ ንዑስ አንቀፅ 3 ተጨምሯል፡፡

10.3. "በማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ዕለት ፈቃደኛ ከሆኑ ከፍተኛ ድርሻ ካላቸዉ ባለአክሲዮኖች መካከል በሚደረግ ስምምነት ወይም ከፍተኛ ባለአክሲዮኖች ፈቃደኛ ሳይሆኑ ሲቀሩ ወይም ጠቅላላ ጉባኤዉ ሌላ ሰዉ ለመምረጥ ሲወስን በጉባኤዉ የሚመረጡ ድምፅ ቆጣሪዎች ቁጥር 3(ሶስት) እንዲሆን ተወስኖአል፡፡

ለ.የመተዳደሪያ ደንብ ማሻሻያ

ሀ. ነባሩ አንቀፅ 6 ተሰርዞ

"ባለአክሲዮኖች የባንኩን አክሲዮን ለመግዛት ከፈረሙት የአክሲዮን ቁጥር ጠቅላላ ዋጋ ላይ እስካሁን ያልከፈሉትን ቀሪ ገንዘብ ይህ ጉባኤ ከተካሄደበት ቀን ጀምሮ እ.ኤ.አ. እስከ ጁን 30 ቀን 2022 ድረስ ከፍለው ማጠናቀቅ አለባቸዉ፡፡ አንድ ባለአክሲዮን በዚህ በተጠቀሰዉ ጊዜ ውስጥ የፈረመዉን አክሲዮን ቀሪ ዕዳ ካልከፈለ የ15 ቀን ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፤በተሰጠዉ ተጨማሪ የማስጠንቀቂያ ጊዜም ካልከፈለ የፈረሙትን አክሲዮን ዋጋ ከፍለዉ ተጨማሪ

ለመግዛት ለሚፈልጉ ሌሎች ባለአክሲዮኖች ወይም የባንኩን አክሲዮን ገዝተዉ የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ኤጀንሲ ቀርበዉ ላልፈረሙ ወይም ሌሎች አስፈላጊ ሰነዶችን ላላቀረቡ ሰዎች ለሽያጭ ይቀርባል፡ይህ ሁሉ ሆኖ ያልተላለፈ/ያልተሸጠ አክሲዮን ቢኖር የማህበሩ አባል ላልሆኑ ሰዎችና በህግ ለተፈቀደላቸው ሰዎች ይሸጣል"፡፡

በሚል አዲስ ተተክቷል፡፡

ለ. አንቀፅ 22(1) መጨረሻ ላይ "ሆኖም የዳይሬክተሮች ቦርድ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኝ ስብሰባዉን በኤሌክትሮኒክ የመገናኛ ዘዴ ሊያደርግ ይችላል፡፡" የሚል ተጨምሮበት ተሻሽሏል፡፡

ሐ. አንቀፅ 23(4) "የሚተላለፉ የገንዘብ ሰነዶችን በተለይም የንግድ ወረቀቶችን የሚተላለፍ የግዴታ ምስክር ወረቀቶችን እና የሽቀጥ ማረጋገጫ ሰነዶችን መፈረም፣ ማስተላለፍና መቀበል ይችላል" ተብሎ ተጨማሪ ሥልጣን ለዋናው ሥራ አስኪያጅ ተሰጥተዋል፡፡

ከላይ የተጠቀሱትን ውሳኔዎች የያዘውን የአስቸኳይ ጉባዔ ቃለ-ጉባዔ በንግድ ሕጉ መሠረት የጉባዔው ሥነ ሥርዓት አስፈጻሚዎች እና የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት የፌደራል የሠነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ኤጀንሲ ቀርበው በመፈረም እንዲያስመዘግቡ ጉባዔው ሙሉ ኃላፊነት ሰጥቷቸዋል፡፡

6.5 የዕለቱን ቃለ ጉባኤ ማፅደቅ

በጉባኤዉ ማጠቃለያ ላይ የጉባኤዉ ሰብሳቢ የዕለቱን ጉባኤ ቃለ ጉባኤ የጉባኤዉ ፀሐፊ በንባብ እንዲያሰሙ ጠየቁ፡፡ የጉባኤዉ ፀሓፊም ቃለ ጉባኤዉን በንባብ አሰሙ፡፡ ጉባኤዉም ቃለ ጉባኤዉን ያለ ምንም ተቃውሞ እና ድምፀ-ታአቅቦ በሙሉ ድጋፍ/ድምጽ አጸድቆ ስብሰባዉ ከቀኑ 5፡30 ላይ ተጠናቀቀ፡፡

7. አባሪ ሠነዶች

ከዚህ ቀጥሎ የተመለከቱት ሠነዶች ከዚህ ቃለ-ጉባዔ ጋር በአባሪነት ተያይዘዋል፡፡

7.1. በጉባዔው ላይ የተገኙ እና የባለአክሲዮኖችን ዝርዝር የሚያሳይ በጉባዔው የመገኘት የማረጋገጫ ሠነድ (Attendance Sheet) 397 ገፅ፣

7.2. በቦርድ ሰብሳቢ የተደረገ የመግቢያ ንግግር 2 ገጽ፣

7.3. የዳይሬክተሮች ቦርድ ለጉባዔው ያቀረበው የውሳኔ ሃሳብ/መግለጫ 2 ገፅ፣

8. የዳይሬክተሮች ቦርድ እና የማህበሩ ጸሐፊ ማረጋገጫ፣

እኛ የጎሕ ቤቶች ባንክ አክሲዮን ማኀበር ዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትና የማህበሩ ጸሐፊ ከዚህ ቃለ-ጉባዔ ሠነድ ጋር አባሪ ሆኖ በተያያዘው የስም መጥሪያ ሠነድ (Attendance Sheet) ላይ ስማቸው፣ የፈረሟቸው እና የከፈሏቸው አክሲዮኖች ብዛት በስማቸው አንፃር ትይዩ በተመለከተው፤ የፈረሙት ባለአክሲዮኖች ሕዳር 28 ቀን 2014 ዓ.ም. በተካሄደው የአክሲዮን ማኅበሩ 1ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ መገኘታቸውን እና ራሳቸው ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በዚህ ቃለ-ጉባዔ ሠነድ ላይ የተገለፁትን ውሣኔዎች ማሳለፋቸውን በሙሉ ስምና ፊርማችን እያረጋገጥን፣ በሠነዶቹ ላይ ስለተገለፁት ጉዳዮች እና ስለተላለፉት ውሣኔዎች ትክክለኛነት ስማቸው በሠነዶቹ ላይ በተዘረዘሩት ሰዎችም ሆነ በሌላ በጉዳዩ ያገባኛል በሚል ወገን ለሚነሳ ማናቸውም የሙብት ጥያቄ ኃላፊዎች መሆናችንን ጭምር እናረጋግጣለን፡፡

24/03/14

ሕዳር 28 ቀን 2014 ዓ.ም.

ተ.ቁ	ስም	በቦርዱ ውስጥ ያለው ኃላፊነት	የቦርዱ አባል ወይም የተወካይ ፊርማ
1	አቶ ጌታሁን ናና ጀንበር	ሰብሳቢ	
2	አቶ ገ/የሱስ ኢጋታ ሲማ	ም/ሰብሳቢ	
3	ዶ/ር ኢ/ር ውብሸት ዠቅአለ መንገሻ	አባል	
4	ወ/ሮ ፋሲካ ከበደ ተመሰለዉ	አባል	
5	አቶ ከፈኒ ጉርሙ ገመዳ	አባል	
6	ወ/ሮ ፅዮን አድማሱ በየነ	አባል	
7	ኢትዮ ላይፍና ጀኔራል ኢንሹራንስ ኢ.ማ. ተወካይ አቶ ሺመልስ ገ/ጊዮርጊስ ሰብስቤ	አባል	
8	አቶ በላቸዉ ሁሪሳ ዳዲ	አባል	
9	ሬድዋ ሞተርስ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ተወካይ አቶ ታደሰ አድማሱ ጠና	አባል	
10	ወይ. መስከረም መለሰ ወርቁ	የማህበሩ ፀሐፊ	

Federal Documents Authentication & Registration Agency (Addis Ababa Branch Twelve Office)

NATIONAL BANK OF ETHIOPIA

አባሪ ፤፡ከዳይሬክተሮች ቦርድ የቀረበ የውሳኔ ሃሳብ

ህዳር 28 ቀን 2014 ዓ.ም

ጎሕ ቤቶች ባንክ አ.ማ
የባለአክሲዮኖች 1ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ
የባንኩን የተፈረመ ዋና ገንዘብ የክፍያ ጊዜ ለማሳጠርና ነባሩን ዋና ገንዘብ ለማሳደግ ከዳይሬክተሮች ቦርድ የቀረበ የውሳኔ ሃሳብ

ሀ. መነሻ ምክንያቶች

አንድ ባንክ በተለያዩ ምክንያቶች ዋና ገንዘቡን ለማሳደግ ሊወስን ይችላል፡፡ ከእነዚህ ምክንያቶች መካከል የባንኩን የሥራ እንቅስቃሴ በዓይነትም በመጠንም ማስፋፋት፣ ወይም በሕግ የተቀመጠዉን አስገዳጅ አነስተኛ የዋና ገንዘብ መጠን ማሟላት፤ ወይም የባንኩን ስጋት የመሸከም አቅም ማጠናከር፤ ወይም በሁለቱ አልያም በሶስቱ ሊሆን ይችላል፡፡ ከእነዚህ ጥቅል የዋና ገንዘብ ማሳደግያ ምክንያቶች በመነሳት ከዚህ በታች በተጠቀሱ የሕግ እና ኢኮኖሚያዊ ምክንያቶች የባንካችንን የተፈረመ ካፒታል የክፍያ ጊዜ ማሳጠር እና ዋና ገንዘቡን/ካፒታሉን ማሳደግ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

1. በአሁኑ ጊዜ ያለዉ የባንኩ የተፈረመ ዋና ገንዘብ/ካፒታል ብር 1,056,210,000 ነው፤ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ባወጣዉና ከሚያዝያ 04 ቀን 2013 ዓ.ም. ጀምሮ ተፈጻሚ በሆነዉ መመሪያ ቁጥር SBB/78/2021 መሠረት የባንኮች ዝቅተኛ የተከፈለ ዋና ገንዘብ መጠን(ካፒታል) ብር 5 ቢሊዮን መሆን አለበት፡፡ ይህን አስገዳጅ ዝቅተኛ የተከፈለ ዋና ገንዘብ መጠን፤
   - ነባር ባንኮች በ5 ዓመት ውስጥ፤
   - እንደእኛ በወቅቱ በመመስረት ሒደት ላይ የነበሩ ባንኮች ደግሞ የባንክ ሥራ ከጀመሩበት ቀን ጀምሮ በ7 ዓመት ውስጥ፤

   ማሟላት አለባቸው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ባንኮች በተሰጠዉ ጊዜ ውስጥ ዝቅተኛዉን የዋና ገንዘብ መጠን የሚያሟሉበትን ሁኔታ በተመለከተ የድርጊት መርሐግብር (action plan) አዘጋጅተዉ ለብሔራዊ ባንክ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

   ስለሆነም ጎሕ ቤቶች ባንክ በህግ የተቀመጠውን ዝቅተኛ የካፒታል መጠን ብር 5 ቢሊዮን ለማሟላት እስከ ጥቅምት 2021 ዓ.ም. ድረስ ቢያንስ ብር 3.95 ቢሊዮን የሚያወጡ አዲስ አክሲዮኖችን መሸጥ ያለበት በመሆኑ፣
2. ባንኩ የሞርጌጅ ባንክ ስለሆነ አትራፊ ሆኖ ለመቀጠል ከፍተኛ ካፒታል ስለሚያስፈልገው፣
3. ባንኩ ተከታታይ ዕድገት እና ትርፋማ ይሆን ዘንድ ከታሰበው ዕድገት ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ስጋትን ሊሸከም የሚችል ካፒታል ስለሚያስፈልገው፤
4. ከነባር ባንኮች እና አዲስ ወደ ገበያው እየገቡ ካሉ ባንኮች ጋር ለመወዳደር የሚያስችል የካፒታል አቅም ለመገንባት፣እና
5. ባንኩ በአለም አቀፍ ደረጃ ካሉ ኢንቨስተሮች (investors)፣ በሪል ስቴት ዘርፍ ከተሠማሩ እና ከአበዳሪ ተቋማት ጋር አብሮ ለመስራት ስለሚገባው እና አንዳንድ አካላት ደግሞ የባንኩን የዋና ገንዘብ ጥንካሬ እንደ መለኪያ ስለሚያቀርቡ ለዚህ በቂ ሆኖ ለመገኘት።

ለ. የውሳኔ ሃሳብ

ከላይ በተጠቀሱት ዋና ዋና ህጋዊና ኢኮኖሚያዊ ምክንያቶች የባንኩን የተከፈለ ካፒታል እስከ ጥቅምት 2021 ድረስ ወደ ብር 5 ቢሊዮን ከፍ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በኢትዮጵያ የንግድ ህግ መሰረት ካፒታል መጨመር የሚቻለው አስቀድሞ የተፈረመው/ቃል የተገባው/ ካፒታል ተከፍሎ ሲጠናቀቅ ነው። በመሆኑም ቦርዱ የሚከተለውን የውሳኔ ሃሳብ ለጉባኤው ያቀርባል፤

<u>**የውሳኔ ሃሳብ 1፡- የተፈረመውን ካፒታል በአጭር ጊዜ ከፍሎ ማጠናቀቅ**</u>

ባንኩ ሲመሠረት ለሽያጭ የቀረቡ እና የተፈረሙ አክሲዮኖች ቀሪ ዋጋ የመክፈያ ጊዜ በባንኩ የመመስረቻ ፅሑፍ እና የመተዳደሪያ ደንብ ላይ እንደተጠቀሰዉ ባንኩ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ በ18 ወራት ውስጥ (እስከ የካቲት 30 ቀን 2015 ዓ.ም ድረስ) ነው። ነገር ግን ይህ ጊዜ ይጠበቅ ቢባል ከላይ ከተዘረዘሩት ምክንያቶች ጋር የተጣጣመ አይሆንም።

በመሆኑም፤ይህ ጊዜ እስከ እ.ኤ.አ. ጁን 30 ቀን 2022 (ሰኔ 23 ቀን 2014 ዓ.ም.) ድረስ እንዲሆንና አፈፀፃሙም በህግ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ እንደሚከተለው እንዲሆን ቦርዱ የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል።

በዚህ ጊዜ እና በሕግ መሠረት በሚሰጠዉ ተጨማሪ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ወስጥ ባለአክሲዮኖች የሚጠበቅባቸውን ከፍለው ካላጠናቀቁ አክሲዮኖቹ ፥

1.1 የባንኩን አክሲዮን ገዝተው ግን በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ኤጀንሲ ቀርበዉ ባለመፈረማቸው ወይም አስፈላጊ ሰነዶችን ባለማሟላታቸዉ ምክንያት ባለአክሲዮን መሆን ላልቻሉ ሰዎች እንዲተላለፉ፥ ወይም
1.2 ተጨማሪ አክሲዮኖችን ለመግዛት ለሚፈልጉ ሌሎች ባለአክሲዮኖች እንዲሸጡ፥ ወይም
1.3 ከላይ በ 1.1 እና በ 1.2 መሰረት ያልተላለፉ/ያልተሸጡ እንደሆነ ለሕዝብ ቀርበው እንዲሸጡ፤

ለቦርድ ሥልጣን እንዲሰጥ ቦርዱ የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል፡፡

የውሳኔ ሃሳብ 2፡- የባንኩን ካፒታል ወደ ብር 3.056 ቢሊዮን ማሳደግ

የባንኩ ህልውና እና ቀጣይነት የሚረጋገጠው ከላይ እንደተገለፀው በህጋዊና ኢኮኖሚያዊ ምክንያቶች የሚያስፈልገውን ካፒታል አሟልቶ ሲገኝ ነው። ባንኩ በህግ ከሚፈለግበት ዝቅተኛ የካፒታል መጠን በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ለመድረስ ጉዞውን አሁን መጀመር አለበት።

ስለሆነም አሁን የተፈረመው ብር 1,056,210,000 ካፒታል ተከፍሎ ሲጠናቀቅና ሙሉ በሙሉ መከፈሉ ሲረጋገጥ 2 ቢሊዮን ብር ዋጋ ያላቸዉ 2 ሚሊዮን አዲስ አክሲዮኖችን በማዉጣት የባንኩ ዋና ገንዘብ ወደ ብር 3,056,210,000 (ሶስት ቢሊዮን ሃምሳ ስድስት ሚሊዮን ሁለት መቶ አስር ሺህ) እንዲያድግና አፈፀፃሙም በህግ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ እንደሚከተለው እንዲሆን ቦርዱ የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል።

2.1. የባንኩ ነባር ባለአክሲዮኖች ከሚወጡት አዲስ አክሲዮኖች ላይ ባላቸዉ ቅድሚያ የመግዛት መብት መሠረት መግዛት የሚፈልጉትን አክሲዮኖቹ ለሽያጭ መቅረባቸው ይፋ ከሆነበት ቀን ጀምሮ በስድስት ወራት ውስጥ ለባንኩ ለዚህ ተብሎ በተዘጋጀ ፎርም ሞልተው እንዲያሳዉቁና የመግዛት ፍላጎታቸዉን በሚያሳዉቁበት ጊዜ የሚገዙትን የአክሲዮን ብዛት ጠቅላላ ዋጋ 25% (ሃያ አምስት በመቶ) እንዲከፍሉ፣
2.2. ባለአክሲዮኖች ለመግዛት የፈረሙትን አክሲዮን ዋጋ እ.ኤ.አ. እስከ ሰኔ 30 ቀን 2025 (ሰኔ 23 ቀን 2017 ዓ.ም.) ድረስ ሙሉ በሙሉ ከፍለዉ እንዲያጠናቅቁ እንዲወሰን፣ እና
2.3. በተጠቀሰው አኳኋን ድልድል ተደርጎ በማናቸውም ምክንያት ሳይሸጥ የቀረ እና/ወይም ተፈርሞ ሳይከፈል የቀረ አክሲዮን ቢኖር ቦርዱ ተገቢ ነው ብሎ በሚወስነው መሠረት እንዲሸጥ እና ከአፈፃፀሙ ጋር ውሳኔ የሚጠይቅ ማንኛውም ጉዳይ ቢኖር ሕግ በሚፈቅደው መሠረት የዳይሬክተሮች ቦርድ እንዲወስንና እንዲያስፈፅም ለቦርድ ሥልጣን እንዲሰጥ።

በመጨረሻም ቦርዱ የተከበረውን ጉባዔ ከላይ የተመለከቱትን ሁለት የውሳኔ ሃሳቦችን ተቀብሎ እንዲያፀድቅ በታላቅ አክብሮት ይጠይቃል፡፡

ጎህ ቤቶች ባንክ
የዳይሬክተሮች ቦርድ

ሕዳር 28 ቀን 2014 ዓ.ም.

አባሪ 2፡ በቦርድ ሰብሳቢ የተደረገ የመግቢያ ንግግር 2 ገጽ

ጎሕ ቤቶች ባንክ አ.ማ.

የባለአክሲዮኖች 1ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ

በዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ የተደረገ የመግቢያ ንግግር

የተከበራችሁ የጎሕ ቤቶች ባንክ ባለአክሲዮኖች
የተከበራችሁ የጎሕ ቤቶች ባንክ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት
የተከበራችሁ ጥሪ የተደረገላችሁ እንግዶች

ክቡራትና ክቡራን!

ጥሪያችንን አክብራችሁ ዛሬ እዚህ በመገኘታችሁ በራሴና በጎሕ ቤቶች ባንክ የዳይሬክተሮች ቦርድ ስም ከልብ አመሰግናለሁ።

በሀገራችን እንደባንክ ያለ የፋይናንስ ተቋምን ማቋቋም በንፅፅር ብዙ ቅድመ ሁኔታዎች ማሟላትን ይጠይቃል፡፡ ባንክን ማቋቋምና ሥራ ማስጀመር ለብዙ ባለድርሻ አካላት ዘርፈ ብዙ ጥቅም ያለው ቢሆንም ሒደቱ ብዙ ውጣ ውረድና ፈተናዎች ያሉበት ነው። የመጀመሪያውና ከባዱ ፈተና ለባንኩ ምሥረታ የሚያስፈልገውን ዝቅተኛ ካፒታል ማሳባሰብና የመስራቾች ጉባዔ ማካሄድ ነበር። በዚህ ሂደት ጎሕ የቤቶች ባንክን ለማቋቋም አክሲዮን ሽያጩ በይፋ ከተጀመረበት ከመስከረም 8 ቀን 2012 ጀምሮ ሽያጩ እስከ ተጠናቀቀበት ነሃሴ 30 ቀን 2012 ድረስ በአደራጆች በተደረገው ከፍተኛ ጥረትና በባለአክሲዮኖች እገዛ ብር 533.8 ሚሊዮን የተከፈለና ብር 1.2 ቢሊዮን የተፈረመ ካፒታል መሰብሰብ በመቻሉ መስከረም 28 ቀን 2013 የመስራቾች ጉባዔ ተካሂዶ ባንኩ ተመሠረተ። ቀጣዩና እጅግ በጣም ከባዱ ሂደት ባንኩን በንግድ መዝገብ ማስመዝገብና የሥራ ፍቃድ ማግኘት ነበር። ይህ ሂደት ከፍተኛ ትዕግሥት የጠየቀ፥ ከተጠበቀው በላይ ረጅም ጊዜ የወሰደና ከታቀደው በላይ ወጪም ያስወጣ ነበር። ሂደቱን ለማጠናቀቅ ከዘጠኝ ወር በላይ ወስዷል። ይህም በመሆኑ ባንኩ ሥራ ለመጀመር ያቀደውን ጊዜም በስድስት ወር ገፍቶታል። ምንም እንኳ ከላይ እንደተጠቀሰው ባንኩ አክሲዮን ሽያጩን ያጠናቀቀው ከ7,883 ባለአክስሲዮኖች በተሰበሰብ ብር 533.8 ሚሊዮን የተከፈለና ብር 1.2 ቢሊዮን የተፈረመ ካፒታል ቢሆንም 1,225 ባለአክሲዮኖች በተለያዩ ምክንያቶች በተደረገላቸው ጥሪ መሰረት በሠነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ኤጀንሲ ፊት ቀርበው በወቅቱ በባንኩ መመሥረቻ ጽህፍና መተዳደሪያ ደንብ ባለመፈረማቸው የሥራ ፈቃዱን ያገኘው በብር 521.5 ሚሊዮን የተከፈለና በብር 1.056 ቢሊዮን የተፈረመ ካፒታል ነው። እነዚህ በባንኩ የአክሲዮን መዝገብ ያልተካተቱ 1,225 ባለአክሲዮኖች የመስራችነት መብታቸው ተጠብቆ በመዝገቡ የሚካተቱበት መንገድ ወደፊት ይመቻቻል። አሁን ላይ የሁላችንም ጥረትና ልፋት ፍሬ አፍርቶ ባንኩ በይፋ ሥራ በመጀመሩ እንኳን ደስ አለን ለማለት እወዳለሁ፡፡

ክቡራትና ክቡራን!

ለዛሬው ጉባዔ መጠራት ዋና ምክንያት የባንኩን ካፒታል ማሳደግ አስፈላጊነት ነው። ከላይ እንደተገለጸው የባንኩ የተፈረመ ካፒታል ብር 1.056 ቢሊዮን ነው። በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ መሠረት የባንኮች ዝቅተኛ የተከፈለ ካፒታል ብር 5 ቢሊዮን መሆን አለበት፡፡ በመሆኑም ይህ ጉዳይ የዛሬው ጉባዔ ዋና አጀንዳ ሆኖ ቀርቧል። ከዚሁ ጋር

በተያያዘና በሌሎች ምክንያቶች በባንኩ መመስረቻ ጽሁፍና መተዳደሪያ ደንብ ላይ ማሻሻያ እንዲደረግ አጀንዳ ተይዟል። ጉባዔው በእነዚህ አጀንዳዎች ተወያይቶ ለባንኩ ቀጣይነት፣ ተወዳዳሪነትና ትርፋማነት በሚበጅ መልኩ እንዲወስን በታላቅ አክብሮት እጠይቃለሁ።

በመጨረሻም ባንኩን ለማቋቋም፣ የሥራ ፈቃዱን እንዲያገኝና ሥራ እንዲጀምር በየራሳቸው የደገፉንን ሁሉንም ባለአክስሲዮኖች፣ የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ኤጀንሲ፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ፣ የባንኩን አደራጆችና የቦርድ አባላት እንዲሁም የባንኩን የማናጅመንት አባላትና ሠራተኞች በራሴና በቦርዱ ስም ከልብ አመሰግናለሁ፡፡ የሞርጌጅ ባንክ ሥራዎች በአብዛኛዉ ለሀገራችን አዲስ በመሆናቸዉ ባንኩን ውጤታማ ለማድረግ ወደፊትም ድጋፋችሁ እንደማይለየን ተስፋ አደርጋለሁ፡፡

አመሰግናለሁ!
ኢትዮጵያ ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር!

ጌታሁን ናና
የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ
ሕዳር 28 ቀን 2014፤ ኢንተር ሌግዠሪ ሆቴል፣ አዲስ አበባ።

አባሪ 3፡ በጉባዔው የመገኘት የማስረጃ ሠነድ (Attendance Sheet) 397 ገፅ

Federal Docum... Agency (Branch Office)
Authentic... Addis Ab...